# ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

የኢፌድሪ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአመራሮችና አስተዳዳሪዎች አሰያየምን ለመደንገግ በወጣው መመሪያ መሰረት ቀጥሎ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የሚያሟሉ እና ዩኒቨርስቲውን በፕሬዚዳንትነት ለመምራት ፍላጎቱና ብቃቱ ያላቸውን አመልካቾች አወዳድሮ መመደብ ይፈልጋል፡፡

1. የስራው መደብ
   1.1. ፕሬዚዳንት
2. ተወዳዳሪዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች
   2.1. የትምህርት ደረጃ:- የሶስተኛ ዲግሪ (PhD) ያላቸው ወይም የሁለተኛ ( Masters) ዲግሪ ያላቸውና በዩኒቨርስቲ ቆይታቸው ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው/ያላት፡፡
   2.2. የስራ ልምድ:- በከፍተኛ ትምህርት፣ በምርምር ተቋማት ወይም መሰል ተልዕኮ ባላቸው ተቋማት በከፍተኛ አመራርነት/ኃላፊነት እርከን የተረጋገጠ ልምድ ያለው/ያላት፣
   2.3. አመልካቾች የሚወዳደሩበትን ዘርፍ በዋና ተግባር ለማሳደግና ለማሻሻል ስለሚከተሉት ስልቶች ከ10 ገጽ ያልበለጠ ስትራቴጂክ ዕቅድ በጽሑፍ የሚያቀርቡና ያቀረቡትን ንድፈ ሀሳብ በሚዘጋጅ መድረክ ላይ ተገኝተው ገለፃ ማድረግና ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ
   2.4. ፆታ: ማስታወቂያው ወንዶችንና ሴቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን ፍላጎቱ ያላቸው ሴት ተወዳዳሪዎች ይበረታታሉ፡፡
3. ተፈላጊ ክህሎቶች
   3.1. አመልካቾች በሚወዳደሩበት ስራ መደብ ያለውን የሰው፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ሀብት በማስተባበር ለመምራት የሚያስችል ክህሎት ያላቸው መሆን አለባቸው፣
   3.2. በሚወዳደሩበት ስራ መደብ ለውጥና እድገትን ለማምጣት የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራር ስልቶችን የማመንጨትና ተግባራዊ የማድረግ አቅም ያላቸው መሆን አለባቸው
   3.3. አመልካቾች የዩኒቨርስቲውን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል የተግባቦት ክህሎት ያላቸው መሆን አለባቸው
4. ተፈላጊ ስነ-ምግባራዊ ባህርያት
   4.1. አመልካቾች ከስነ-ምግባር ጉድለቶች የፀዱ፣ በመልካም ባህርያቸውና ታታሪነታቸው የተመሰከረላቸውና ለሌሎች አርአያነታቸው የጎላ መሆን አለባቸው:፤
   4.2. አመልካቾች ተግባብቶ የመስራት፣ ሁሉን በእኩል የማስተናገድ፣ ለሚቀርቡላቸው ጉዳዮች ተገቢውን ምላሽ በተገቢው ጊዜ የመስጠት መርህ የሚከተሉ መሆን አለባቸው:፤
5. የምደባ ሁኔታ

   በውድድሩ የላቀ ውጤት በማምጣት የተመረጠው/ችው አመልካች በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ለስድስት አመታት በፕሬዝዳንትነት የሚያገለግል/የምታገለግል ይሆናል፡፡
6. ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም

   በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስኬል መሰረት
7. የማመልከቻ ጊዜ

- ✓ አመልካቾች ማመልከቻቸውን CV እና ኦርጅናል የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃቸውን እንዲሁም ከ10 ገጽ ያልበለጠ ስተራቴጂያዊ እቅድ ከማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር ማስታወቂያው ***ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 10 የስራ ቀናት*** ውስጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

8. ***የማመልከቻ ቦታ***

**የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ግዥ ዳይሬክቶሬት የሚገኝበት ህንጻ 2ኛ ፎቅ በሚገኘው የዩኒቨርስቲው የፕሬዝዳንት ምልመላና ምርጫ ኮሚቴ ጊዜያዊ ቢሮ ቁጥር R-205 በአካል በመቅረብ ማቅረብ ይችላሉ::**

9. ***የማመልከቻ ማቅረቢያ መንገዶች***

   9.1. **የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ግዥ ዳይሬክቶሬት የሚገኝበት ህንጻ 2ኛ ፎቅ በሚገኘው የዩኒቨርስቲው የፕሬዝዳንት ምልመላና ምርጫ ኮሚቴ ጊዜያዊ ቢሮ ቁጥር R-205 በአካል በመቅረብ ማቅረብ ይችላሉ::**

   9.2. **ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀው የኢ-ሜይል አድራሻ** presidentmtu@gmail.com

   9.3. **በፖስታ ሳጥን ቁጥር** 260 **ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ አድራሻ በመላክ**

***ለተጨማሪ መረጃ***

- ➢ **ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀው የኢ-ሜይል አድራሻ** presidentmtu@gmail.com
- ➢ **በስልክ 0910906749**

***ማሳሰቢያ:-***

- ✓ **አመልካቾች አስፈላጊውን ሰነዶችን በፖስታ በማሸግ ስም፣ ስልክ ቁጥርና ኢ-ሜይል በመጥቀስ በተቀመጠው ጊዜና ቦታ መረጃቸውን ማቅረብ አለባቸው::**

***የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ስራ አመራር ቦርድ***